# የመጽሐፍ ግምገማ

# የተቀናጀ ንባብ በበዕውቀቱ ሥዩም *የማለዳ ድባብ* የግጥም መድብል

**አንተነህ አወቀ**[1]

**የግጥሙ መድብል - *የማለዳ ድባብ***
**ደራሲ - በዕውቀቱ ሥዩም**
**የህትመት ዘመን - 2009 ዓ.ም.**

*የማለዳ ድባብ* መድብል ውስጥ የተካተቱት ብዙዎቹ ግጥሞች በመጽሐፍ መልክ ከመታተማቸው በፊት በማህበራዊ ሚዲያዎች ለንባብ የበቁ ናቸው። የመጽሐፉ ግምገማ መጽሐፉ በታተመበት ዘመን ገጣሚው በእውቀቱ በሚገኝበት ይቀርባል ተብሎ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

የዳሰሳው ርእስ "የተቀናጀ ንባብ" የተባለበት ምክንያት በመድብሉ ግጥሞች ላይ ውስጣዊም ውጫዊም ንባብ ለማድረግ በሞመከሩ ነው። ውጫዊ ንባብን አስመልክቶ ከፍልስፍና እና ከሌሎች ቴክስቶች ጋር ለማገናዘብና ለመረዳት ተሞክሯል። ትንተናው ከመድብሉ የፊትና የጀርባ ሽፋን፣ ግጥሞቹ ከሚያንጸባርቁት ፍልስፍና፣ ግጥሞቹ ከሚጠሯቸው ቴክስቶችና ከቀረቡበት ስልት፣ እንዲሁም ከሚያንጸባርቁት ይዘት አንጻር ለማየት ተሞክሯል።

**የውጭ ሽፋን**፡- እንደ ርእሱ ሁሉ የማለዳ ድባብን የሚያሳይ ነው። ጎህ የቀደደበት ይመስላል። ብሩህ ገጽታ አለው። ድባብ የያዙ የክት/የማእረግ ጸአዳ ልብስ የለበሱ ሰዎች (ካህናት) የሚታዩበት የተፈጥሮ አካበቢ ነው። ካህናቱ በማለዳ የጸሎት ሥርዓት፣ አለበለዚያም በጥዋት ጉዞ ላይ ያሉ ይመስላል። የጥምቀት ሥርዓትን የሚያስታውስም ይመስላል።

ግጥሞቹ ሲነበቡ ግን እንደውጨ ሽፋን ገጽታና ቀለም ብሩህ ደባብን አይፈነጥቁም። ጭጋግ የተጫናቸው ናቸው። ምናልባትም እንደውስጥ ገጹ ሽፋን ስእል ብሩህነታቸውን የተነፈጉና የማህበረሰባችንን ሰቆቃ የሚገልጹ ናቸው። የትውልዱን መከራ እና ተስፋ መቁረጥ የሚያላዝኑ ግጥሞች ናቸው። የመድብሉ የጀርባ ሽፋን ላይ የቀረበው ግጥም ሃሳቡን ቁልጭ አድርጎ እንዲህ ይገልጸዋል፤

> ያው እንግዲህ ጎህ ቀደደ፣ ታሪክ ሆነ የሌት ጣሙ
> አለሎ እንደሚገፋ ጉንዳን ሲባዝን ነው አለሙ
> የማለዳ ሰማይ ቢያምር ቢማርክም ቀለሙ

[1] ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ, ኢሜል: antenehaweke2014@gmail.com

ሲያዩት ድባብ ቢመስልም የቀንበር ያህል ነው ሸክሙ፡፡

የግጥሙ ሃሳብ በተቃርኖ የተሞላ ነው፡፡ ጎህ መቅደድ በተለምዶ የተስፋ፣ ሌት (ጨለማ) ደግሞ የመከራ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በግጥሙ ግን ሌት ጣዕም ያለው፣ ጎህ ደግሞ የስጋት፣ የሸክም መግለጫ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ጉንዳን የታታሪነት ተምሳሌት ነበር፤ በግጥሙ ግን ጉንዳን ባዛና ሆኖ ነው የተሳለው፡፡ ምናልባትም እንደ ግሪኩ አፈታሪክ ንጉስ ሲሲፈስ[2] ትልቅ ቋጥኝ ከመሬት ወደ ተራራ ጫፍ በከንቱ ሲገፋ የሚውል ነው - ጠብ ለማይል ኑሮ፡፡ የዘመኑ ትውልድም እንዲሁ ነው፡፡ በግጥሙ እንደተሳለው የማለዳ ሰማይ ድባብ ቢያምርም፣ የማያምር አንዳች ቀንበር የተሸከመ ይመስላል ተብሎ በተቃርኖ ነው ነው የቀረበው፡፡

ወደ ዋናዎቹ ቴክስቶች ስንገባም ብዙዎቹ ግጥሞች ይህን የኑሮ ሸክም፣ ይህን የህይወት መባዘን ነው የሚገልጹት፡፡ የተለዩ አሉ ካልንም በመድብሉ ሽፋን መግለጫ ሆኖ በቀረበው ግጥም መረዳት እንደሚቻለው ጥርጣሬና እምነት ማጣትን ነው የሚያሳዩት፡፡ አንዳንዴም መልካም የሚመስሉን ነገሮች እንኳን መልካምነታቸውን ለመቀበል ይቸግረናል፡፡ እንጠራጠራቸዋለን፡: ለምሳሌ እነዚህን ስንኞች እንመልከት፤"ጎህ ገስግሶ ደርሶ ጽልመት ቢያባርርም / የማለዳ ድባብ ህብሩ ገጹ ቢያምርም / ሰው ጸሀይን አምኖ ፋኖሱን አይሰብርም፡፡" ይህ ማለት ዘላቂ ሰላም፣ ዘላቂ ደስታ የለንም፡፡ በአጭሩ ግጥሞቹ ግጥምና የዘመን መንፈስ በሚለው ሀተታ መግቢያ እንደተገለጸው የአብዛኛውን የዘመኑ ወጣት ትውልድ ‹‹መንፈስ›› የተገለጠባቸው ናቸው፡፡ ቃናው የጠፋበትን ቅኝቱ የተበላሸበትን የዘመኑን ትውልድ አበሳ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለዘህ እንደ ማሰረጃ "የተካደ ተውልድ" የምተለዋን ግጥም ማንበብ ይቻላል፡፡

*የማለዳ ድባብ* ግጥሞች እውነተኛ የህይወት ተሞክሮ (lived experience) የተገለጸባቸው ግጥሞች ናቸው፡፡ የገጣሚውም ሆነ በአጠቃላይ ገጣሚው የኖረበት ማህበረሰብ ኑሮ ነው የተገለጸባቸው፤ የትውልድ ሰቆቃ ነው የተገለጸባቸው፡፡ የግጥም ተናጋሪው (እንበል ገጣሚው) ራሱን አግሎ ሳይሆን የሰቆቃው ተጋሪ ሆኖ ነው የቀረበው፡፡ በመድብሉ "እኔነት" እና ፣"እኛነት" የነገሰባቸው ግጥሞች መብዛቱም በዚሁ ምክንያት ይመስለኛል፡፡ የሌላውን ችግር አንደራሱ ችግር እያየ ነው ያቀረበው፡፡ ገለልተኛ አይደለም፡፡ ባጭሩ የትውልዱ አፍ ነው የሆነው፡፡ "ሃውልቴ ገናና"፣ "ሙሾ ላመለጠ ወጣትነት"፣ "እኛ"፣ "ደስታ ቢራቢሮ"፣ እና "የተካደ ትውልድ" ሁሉም የገጣሚውን ትውልድ መራራ ህይወት የሚገልጹ ናቸው፡፡ ራሱም የመራራው ገፈት ቀማሽ ነው፡፡ ለምሳሌ "እኛ" የሚለው ግጥም (ከላይ እንደተገለጸው) ስለስደት የሚያወሳ ሲሆን ‹‹ማን ነው የጫነብን መውጫ የለሽ ኑሮ›› በሚለው ስንኝ እንደሚስተዋለው ራሱን የችግሩ ሰለባ አድርጎ ነው ያቀረበው፡፡

[2] ሲሲፈስ በግሪክ አፈታሪክ ከሞተ በኃላ አማልክቱን አታሎ በዚች ምድር ለመቆየት በመሞከሩ ትልቅ ቋጥኝ ዘወትር ወደ ተራራ ጫፍ እየገፋና መልሶ እየተንከባለለበት፣ መልሶ እየገፋ እንዲኖር ተፈርዶበታል (World History Encyclopedia).

"ደስታ ቢራቢሮ" የሚለው ግጥምም ቢሆን የግጥሙ ተናጋሪም እንበል ደረሲው የወጣቱን ችግር እንደታዛቢ ሳይሆን ችግሩ ራሱ እንደሚሰማው አድርጎ ያቀረበበት ነው፡፡ የግጥሙ ተናጋሪ በቁጭት የሌላውንም ቁጭት ያሳየናል፡፡ ቢራቢሮ የህይወት ተምሳሌት ነችና ደስታን ሲያሳድዱ ህይወታቸው በከንቱ የሚባክንባቸውን የትውልድ አባላት ቁጭት ያሳየናል፡፡ ግጥሙ የጸጋየ ገብረመድህንን "ይነግርሃል አንዳች እውነት" የተሰኘ ግጥም መንፈስ ይጋራል፡፡

**በይነአሃዳዊነት** (Intertextuality)

ከመድብሉ ጥቂት የማይባሉ ግጥሞች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሌሎች ግጥሞች ተጽእኖ ያረፈባቸው ናቸው፡፡ ርእሳቸውን እንኳን ብናይ "ሙሾ ላመለጠ ወጣትነት" እና "ሙሾ ለከሰመች ተፈጥሮ" የሚሉት ግጥሞች "ሙሾ ለአማዲዎስ ሞዛርት" የሚለውን የሰይፉ መታፈሪያ ግጥም ያስታውሱናል፡፡ "ደስታ ቢራቢሮ" የጸጋየ ገብረመድህንን "ህይወት ቢራቢሮ"፣ "የቴዎድሮስ ማመንታት በመቅደላ" በድጋሚ የጸጋየ ገብረመድህንን "የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ" ያሳስባል፡፡ "በረከተ መርገም ፪" የኃይሉ ገብረዮሃስን (ገሞራው) "በረከተ መርገም" እንድናስታውስ ያስገድደናል፡፡ "እንጉርጉሮ" የሚለው ግጥም ደግሞ የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምን "እንጉርጉሮ" እና "ዛሬም እንጉጉሮ" የግጥም መድብሎች እና ግጥሞች እንድናስብ ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ ‹‹መኖር ወይስ አለመኖር›› የሼክሲፒር ገጸባህርይ የሐምሌትን መነባንብ ("To be, or not to be") ወይም የጸጋየን አቻ ትርጉም ("መሆን ወይም አለመሆን") ቢያንስ በቅንብሩ ያስታውሰናል፡፡ "ሰቆቃወ በዕውቄ" የጸጋየን "ሰቆቃወ ጴጥሮስ" ያስታውሰናል፡፡ "እኔ እወድሻለሁ" ከገብረ ክርስቶስ ደስታ ግጥም አዝማች የተወሰደ መሆኑን ራሱ በዕውቀቱ በግጥሙ ይነግረናል፡፡ በአጠቃላይ የበእውቀቱ የመድብሉ ጥቂት የማይባሉ ግጥሞች በቅርጽ፣ በይዘት፣ በድምጸት ካለመዷቸው ግጥሞች በመንፈስ የተዋረሱ የተጋቡ ናቸው፡፡

**ትርጉም**

የመድብሉ ጥቂት ግጥሞች ደግሞ ከታዋቂ የውጭ ገጣምያን የተመለሱ ወይም መነሻ አድርገው የተጻፉ ናቸው፡፡ "ከዚህ ወዲያ አልወድሽም" እና "ህልሜን አደራ" ከዊልያም በትለር "Tonight I Can Write the Saddest Lines" እና "The clothes of Heaven" ከሚሉት የተወሰዱ ናቸው፡፡ "ግን አንድ ሰው አለ" የሚለውም ከዊሊያም በትለር ግጥም የተመለሰ መሆኑን ራሱ ገጣሚው ይነግረናል፡፡ በተመሳሳይ "አንሶላዬ ውስጥ ልሙት" ከይሁዳ አማካይ "I Want to Die in my Own Bed"፣ "የምሪ በዳ በረከት" ከኦማር ካያም "Rubaiyats" የተመለሱ ሲሆኑ "መኖር ወይስ አለመኖር" ከዊሊያም ሼክስፒር ገጸባህርጤ ሐምሌት መነባንብ የተጠለፉ ናቸው፡፡ ብዙዎቹን ደራሲው በግልጽ ከየትኛው ደራሲ እንደተወሰዱ ይነግረናል፡፡ የበዕውቀቱን አንባቢነት ያሳዩናል፤ የታዋቂ ገጣምያንን ለአማርኛ አንባቢያን ማስተዋወቁም አንድ ቁም ነገር ይመስለኛል፡፡ አንዳንዶቹ በይዘትም ከኛ የኑሮ ዘይቤ የሚዛመዱ ናቸው፡፡

**በመድብሉ የሚንጸባረቁ ፍልስፍናዎች**

“እውነት እንደሎሌ” (ገጽ 18-19) የሚለው ግጥም ፍልስፍና አዘል ነው፡፡ ገጣሚው ስለእውነት የተፈላሰፈበት ነው፡፡ “እውነት የአሸናፊዎች ናት” / “ኃይለኛ እውነትን ያበጃል” እንዲሁም “እውነት አንጻራዊ ናት” የሚለውን ፍልስፍና ያስተጋበል፡፡ ሰላም በስብከት ሳይሆን በኃይል/በጦርነት ነው የሚሰፍነው ወይም ሰላም ከጦርነት ይመነጫል፡፡ እውነትና እውቀት ከስልጣን ይመነጫሉ የሚሉትን ፍልስፍናዎችን ያስተጋባል፣ይህንም ከሚከተሉት ከ“እውነት እንደሎሌ” ግጥም ስንኞች መረዳት ይቻላል፤

‹‹በወትሮ ልማዱ፣ ሰው መተራረዱ፣ ፈጽሞ ባይቀርም

አንዱ ተሸንፎ አንዱ እንደሚያሸንፍ አያጠራጥርም

ያሸነፈው መስፍን በትንቢቱ ታምኖ ደስ ብሎት ሲሾመኝ

የተሸነፈው ግን ያልሁትን አስቦ እኔን መቅጣት ቢመኝ

ከምኞት ባለፈ ከቶ ምን ያመጣል

የተሸነፈ ሰው ስልጣኑን ያጣ ቀን ሁሉን ነገር ያጣል፡፡

በዚች የጉድ ምድር መሸነፍ ነው ወንጀል፣ ይህንን አውቃለሁ

የተረታ ድኩም፣ ራሱን ሊያጥናና፣ እውነት ያሸንፋል ሲለኝ እስቃለሁ

ይልቅ አሸናፊው እውነትን ያበጃል ባምሳሉ ጠፍጥፎ

ሲሻው ያወርሳታል፣ ለቀጣዩ ትውልድ፣ በጽላት ላይ ጥፎ

ይኸው ግጥም ከላይ ከተገለጸው ፍልስፍና በተጨማሪ “ሰው በተፈጥሮ ጨካኝ/አግረሲቭ/ ነው” የሚለውን ስነልቡዊ ፍልስፍና[3] ያስተጋባል፡፡ ይህንን ሀሳብም “ለመግደል ለመስለብ፣ እጅግ የቋመጠ፣ ሰራዊት መልምለው / ጠመንጃ ወልውለው፣ ሰይፋቸውን ስለው፣ ጩሬውን አሹለው / ዛቻ ተለዋውጠው፣ ለመተናነቂያ፣ የማይቀር ቀን ቆርጠው / ለፍልሚያ ለግልቢያ፣ የተመቸ ስፍራ፣ ድልድል ሜዳ መርጠው” ከሚሉት ስንኞች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስንኞቹ የሰውን “አውሬነት” የሚገልጹ ሲሆን በተለይም “ያዳም ልጆች ልብም ጠንሳሽ የሚጠብቅ የጠብ ድፍድፍ በርሜል” (ገጽ 19) ነው የሚለው የስንኝ ሃሳብ በሚገባ ፍልስፍናውን ይገልጸዋል፡፡

[3] ስለሰው የጨካኝነት/አግሬሲቭ/ ባህሪ አንድ ወጥ አመለካከት የለም፡፡ አንዳዶች ከስነልቡና አንጻር ሲያዩት አንዳንዶቹ ደግሞ ከአካባቢ ተጽእኖ አንጻር ሊያዩት ይሞክራሉ፡፡ ሁሉም የስነልለቡና ባለሙያዎች አንድ አይነት አመለካከት ባይኖራቸውም ጨካኝነት የሰው ተፈጧዊ ባህሪ ነው የሚሉ የፍካሬ ልቡና ሳይንስቲስቶቸ አሉ፡፡ ፍሮይድ እንኳን ብንወስድ የሰው ጨካኝነት ከህይወትና ሞት “ድራይቭስ” እንደሚመነጭ ይጠቅሳል፡፡(Archer፣ 2009)፡፡

ከላይ ከቀረቡት ፍልስፍና ሃሳቦች በተጨማሪ "በሞቷ ፊት ለፊት" (ገጽ 44) የሚለውም ግጥም "የነገረ ህላዌ" ፈላስፎችን "ሰው የሚኖረው ከሞት ጋር ነው" የሚለውን ፍልስፍና እንዲህ ሲል ያሰተጋባል፤

በፍራሻችን ስር፣ ቃሬዛ ተጣብቆ

በልብሳችን ገበር ከፈን ተደብቆ

የእድሩ ጥሩንባ፣ ከሙዚቃው ልቆ

በዘንድሮ ጣቶች ከርሞ ላይነካ

ደህና ሰንብች ማለት ዘበት ኑሯል ለካ፡፡

ግጥሙ የገጣሚውን የህይወት ገጠመኝ መሰረት አድርጎ የተጻፈ ሲሆን መታሰቢያነቱም ሊወልዱ ሀኪም ቤት ገብተው በሞት ለሚለዩት እናቶች የተበረከተ ነው፡፡

በተመሳሳይ "የመኖር ትርጉሙ" በሚለውም ግጥም ብካይ ኑሮን ይገልጻል፡፡ ነገረ ኀላዌ ፈላስፎች ኑሮን አጨልመው ነው የሚያዩት፡፡ የአንደኛና ሁለተኛ ዓለም ጦርነቶች ያስተማሯቸው ፍልስፍና ነው፡፡ በዕውቀቱም "የተካደ ትውልድ" በሚል ግጥሙ (ገጽ 45)፣ "እድሜ ይፍታህ ተብሎ የተወለደ ለት፣ / አምባሩ ካቴና ማተቡ ሰንሰለት›› ሲል የመኖርን ፍሬቢስነት ይገልጽልናል፡፡

በተመሳሳይ "የመኖር ትርጉም" በሚለው ግጥሙ ሰው ሲወለድም ያለቅሳል ሲሞትም ያስለቅሳል፡፡ ይለናል፡፡ መኖር የእንባ ቅብብል ነው ይለናል፡፡ መከራን መግፋት ዕጣችን እንደሆነ ሁሉ፡፡ ሙሉ ግጥሙ እንዲህ ይነበባል፤ "የመኖር ትርጉሙ የንባ ቅብብል ነው፣ በትውልዶች መሃል / አባትህ ያነባው ላንተም ይደርስሃል / ሰው የሆንሁ ለታ ደርሶኛል ይህ እጣ / አልቅሼ እንደገባሁ / አስለቅሼ ልውጣ፡፡"

የበእውቀቱ "ከተለየሽ ወዲያ" የሚለው ግጥም ደግሞ "የጊዜን ሃያልነት" ያሳየናል፡፡ "የጊዜ እንጂ የሰው ጌታ የለውም" እንዲሉ ሁሉ ነገር በጊዜ መዳፍ ውስጥ መሆኑን የሚል ጭብጥ ያዘለ ግጥም ነው፡፡ ግጥሙ የጊዜን ሃያልነት ነው የሚያሳይ፤ ዛሬ አይበገሬ መስሎ የሚታየው ነገ ትቢያ ሲልስ ይታያል፡፡ የሚሻለው በጊዜ ሂደት መልካም ሆኖ መገኘት ነው፡፡ ትናንትናና ዛሬያችን ነው ነጋችንን የሚወስነው፤ KARMA የሚለው የቡዲስቶች ፍልስፍና የሚገልጸው እውነት ይህንን ነው፡፡ ግርጌ ማስታወሻው ይህን እውነት ይገልጸዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ግዜ ተለዋዋጭ ነው፡፡ በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም፡፡ የነበረው እንዳልነበረ መሆኑ አይቀርም፡፡ የግሙ ስንኞች እንዲህ ይነበባሉ፤

ባለት አጥር የከለሉት

የማይጣስ ጥሶ ሾልኮ

በብረት ጣት የጨበጡት

ከመዳፍ ሥር አፈትልኮ

ምንም ነጻ መስሎ ቢታይ

ሁሉም የጊዜ ግዳይ

ሁሉም የጊዜ ምርኮ፡፡

“የነበረው እንዳልነበረ” የሚለው ሃሳብ በማለዳ ድባብ የግጥም መድብል “ወዴት” (ገጽ 70) በሚለውም ግጥም በኢትዮጵያ ተምሳሌትነት ቀርቧል:: ትናንትናችንና ዛሬያችን ካላማረ ሀገር ነው የምትጠፋው፤ የቀድሞ አንድነቷን፣ የቀድሞ ግዛቷን ፣የቀድሞ ታሪኳን የቀድሞ ሃያልነቷንና ስልጣኔዋን ይዛ ልትዘልቅ አትችልም፡፡

በመድብሉ ምናልባትም ተስፋን የሚናፍቅ ብቸና ግጥም (ቢያመነታም) “ተስፋ እንደ ምትሃት” (ገጽ 42) የሚለው ግጥም ነው፡፡ ምናልባትም ከመድብሉ ተስፋን የሰነቀች ብቸኛ ግጥም ነች፡፡ የግጥሙ ተናጋሪ ተስፋን (የምትሃት ያህል እውን መሆኗን ቢጠረጥርም) ተስፋ ሲያደርግ እናነባለን፡፡ ንጋትን መርግ እንደተጫነባት ማላዳ ሳይሆን ትናንቱን እንደምትቀይር ትንሳኤ አድርጎ ለማየት ይሞክራል፡፡ “ነጋ / የግዜር ስውር መዳፍ” ይልና ቀጥሎም “ጨለማውን ስቦ፣ በወግ በሸለላ / ሰማይ የጠፈር ዓይን፣ ብርሃን ተኳለ / ከዶሮ ጩኸት ውስጥ፣ አዲስ ጎህ ተወልዶ / ፍጥረቱ በሙሉ፣ ማርያም ማርያም አለ” ማለት ሀሳቡን ያስረግጣል፡፡

**አንጻር**

የግጥሞቹን አንጻር ስናይ “ልረሻሽ እየጣርኩ ነው”፣ “መዓዛሽ ፈወሰኝ”፣ “ሙሾ ላመለጠ ወጣትነት”፣ “ላባቴ”፣ “እኔ ወድሻለሁ”፣ “በዝግ በር”፣ “ህልሜን አደራ”፣ “መትረፌ ገረመኝ”፣ “አንሶላዬ ውስጥ ልሙት” ፣ “ከተለየሁሽ ወዲያ” … የሚሉት ግጥሞችና እና ሌሎች (ከሶስት እጅ በላይ) በአንደኛ መደብ ‹‹እኔ›› ነው የቀረቡት፤ ምናልባትም ገጣሚው የትውልዱን ሰቆቃ ተጋሪ እንጂ ታዛቢ ብቻ አለመሆኑን የሚያሳዩ ይመስላሉ፡፡

በዚህ አንጻር በቀረቡት ብዙዎቹ ግጥሞች እኔ ባይ ገጸሰቦቹ antihero (ተራና አልባሌ) ናቸው፡፡ የ‹‹እኔነት›› ተስፋቸው የጨለመ፣ የኑሮ መርግ የተጫናቸው፣ በኑሯቸው የሚያላዝኑ፣ ለትውልድ መልካም አሻራ ሊተዉ ቀርቶ ለራሳቸው ህልውና አስተማማኝ መሰረት የሌላቸው ባዶ እኔዎች ናቸው፡ ፡ ለአስረጂ ‹‹**ሙሾ ላመለጠ ወጣትነት**›› የሚለውን ግጥም ማናበብ ይቻላል፡፡

**ቀልድ/ለዛ/ሂዩመር**

ብዙዎቹ ግጥሞች የትውልዱ ሰቆቃ የተገለጸባቸው ቢሆኑም በሂዩመር የታጀቡ በመሆናቸው ፈገግ ማስደረጋቸው አይቀርም፡፡ለምሳሌ፡-

እኔ እወድሻለሁ፣

ጦም ውሎ እንደመጉረስ

ወልዶ እነደመታረስ

ቶምቦላ እንደመድረስ

ካላሙዲ ንብረት

ግማሽ እንደመውረስ

የሚለውን ግጥም ስናይ የመጀመሪያዎቹ የደስታ ምንጮች ተርቦ መጉረስና ወልዶ መታረስ በእርግጥም የወል የደስታ ምንጮች ሲሆኑ ቶምቦላ መድረስና ያላሙዱንን ሃብት መመኘት ግን በተቃርኖ የመጡ የስራ ውጤት ያልሆኑ ለቢልት የገቡ ቁም ነገር የሌላቸው ተግባራቸው ፈገግታን ማጫር ብቻ የሆነ አገላለጾች ናቸው፡፡ እንዲህ አይነት ከግጥሞቹ በሃሳብ ብዙም ስምረት የሌላቸው ፈገግ ለማሰኘት ብቻ የገቡ በርካታ ስንኞች በብዙ ግጥሞች ውስጥ ይገጥሙናል፡፡ ኮስተር ያለ ቁም ነገር ላይ ፈገግ የሚያስደርግ ቃል ሀረግ ሃሳብ እንደ ዋዛ ጣል አድርጎ ማለፍ አንባቢን ምቾት ይሰጠዋል ብየ እገምታለሁ፡፡

ከላይኛው በተመሳሳይ ‹‹ጠብ እና ጥበብ›› የሚለውም ግጥም ሂዩመር የተመላበት ይመስለኛል፡፡ ሽሙጥም ይመስላል፤

ተዋጋ ብሎ ቢሰጠው ጋሻ

ለናቱ ሰጣት የእበት ማፈሻ፡፡

የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ጠብን መፍራት

ጦርን መግራት

ከጋሻ የእበት ማፈሻ መሥራት

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች የቀረርቶ ግጥሞች ናቸው፡፡ ለጣቂዎቹ ስንኞች የሀገርኛውን ቀረርቶ ሃሳብ የሚያጠይቁ ናቸው፡፡ ምናልባትም የሚሳለቁ - በተቃርኖ! የመጽሐፍ ቅዱሱን ጥቅስም መነሻ በማድረግ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ጦርን መፍራት ነው፡፡ ይለናል፡፡ በእርግጥ እንደቀረርቶው አላነወረውም፣ አልተሳለቀበትም፡፡ እግዚአብሄር አመጻንና ጦርን አያበረታታምና!

**መቼት**

የበእውቀቱ ብዙዎቹ ግጥሞች የአዲስ አበቤን ኑሮ የሚገልጹ ናቸው፡፡ አዲስ አበባ በየአጋጣሚው ትነሳለች፡፡ ‹‹መዓዛሽ ፈወሰኝ››(ገጽ 20)፣ ‹‹እንደምነሽ ሻገር›› (ገጽ 64)፣ ‹‹ሰቆቀወ በዕውቄ›› (ገጽ 84)፣ በሚሉት ግጥሞች ብሶት ይገለጽበታል፤ የከተማዋ ጉድፍ ይዘከርበታል፡፡ ከተጠቀሱት ግጥሞች አንዱን ወስደን ጥቂት ስንኞችን እንደማስረጃ መጠቀሱ በቂ ነው፡፡ ለምሳሌ የ‹‹መአዛሽ ፈወሰኝ›› ስንኞች “እንዲያው ሲፈርድብኝ፣ ቤቴ አዲስ አበባ / ሰማዩ ጥንብ ነው፣ መሬቱም አዛባ / ዓይን ጆሮ ምላስ፣ ለኑሮ ሳያንሰኝ / ምን በድየው ጌታ፣ አፍንጫ ለገሰኝ፡፡” በማለት ይተቻሉ፡፡ የ‹‹ሰቆቀወ በዕውቄ›› ከተሰኘው ግጥም ደግሞ “ስፈሬ ሃያ ሁለት ማዞርያ ሆይ / ፎቅን በፎቅ ላይ ሲደርቱ የተመረጡቱ / ጠጠር ዘርተው ወርቅ ሲያጭዱ / ያላረሱትን ሲያመርቱ ” እና በተቃራኒው “ሃያ ሁለት ማዞርያ ሆይ / አያቴ ላንቺ አልሞተም?” ቀጥም “ላንች ክብር አልመከተም? / ታዲያ አሁን ምነው መዳፍሽ ገፋን / የእንጀራ ልጅ ይመስል” የሚሉት ስንኞች የነዋሪው ብሶት የሚገልጹ ናቸው፡፡

በዚህ አጋጣሚ መድብሉ አዲስ አበባንና አዲስ አበቤዎችን ሲመለከት የገጠሩን ህይወት ችላ ያለው ይመስላል። በተፈጥሮ ላይ ያተኮሩ ጥቂት ግጥሞች ቢኖሩም (ለምሳሌ ‹‹ሙሾ ለከሰመች ተፈጥሮ›› (ገጽ 90 - 91) ከመልካም ገጽታዋ ይልቅ መራቆቷ ነው የተገለጸበት።

### ተቃራኒ ገጽታዎች

መዓዛሽ ፈወሰኝ በሚለው ግጥም የአዲስ አበባ ወጣት ሴቶች ውበት ከአዲስ አበባ ከተማ ውበት ተቃርኖ ቀርቧል። የሴቶቹን ውበት ‹‹አንገትሽ ሺነት ዛፍ፣ ጡትሽ ደብረ ከርቤ›› እየተባለ ሲወደስ የሴቶቹ መኖሪያ አዲስ አበባ ግን ‹‹ሰማዩ ጥንብ ነው፣ መሬቱም አዛባ›› እየተባሉ ተጣጥሎ ቀርቧል። ‹‹ላባቱ›› በሚለው ግጥም ደግሞ አባት ‹‹ደሃ ግን ኩሩና ጠንካራ››፣ ‹‹መልካም/ትሁት ግን አትንኩኝ ባይ››፣ ‹‹ሰው ግን መላክ›› ተደርገው በተቃርኖ ተገልጸዋል፡

‹‹ከልጅነት ፍቅር›› በሚለው ግጥሙ ‹‹ለውጥና አለመለወጥ›› በተቃርኖ ቀርበዋል። ወይ ገራምነቴ በሚለው ግጥም ምድራዊውና ሰማያዊው (አውቶቡስን ትቼ መሲህ መጠበቁ በሚል ፈሊጥ) በተቃርኖ ቀርቧል።

‹‹ልረሳሽ እየጣርኩ ነው›› (ገጽ 22) በሚለው ግጥሙ ትዝታን ለመርሳት የሚያደርገውን ሙከራ እንዳልነበረ ሁሉ ‹‹ትዝታን ባኀበር›› (ገጽ 63) በሚለው ግጥሙ ደግሞ መርሳት አለመቻሉን በተቃርኖ ያስነብበናል።

### ፖለቲካ

የበዕውቀቱ *የማለዳ ድባብ* ግጥሞች ቁጥቸው ቀላል የማይባሉት ፖለቲካ ነክ ናቸው። በሀገር በህዝብ ጉዳይ ላይ የተጻፉ ናቸው። ለምሳሌ ‹‹አገሬ›› እና ‹‹ስለጦቢያ የተነገረ ሽክም›› የሚሉት ግጥሞች ጥሩ ግንዛቤ ይሰጣል። ‹‹አገሬ›› በተሰኘው ግጥም ከኤርትራ መገንጠል ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ የባህር በር ማጣት ጉዳይ የተገለጸበት ሲሆን ለባህር በሯ መከበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የነበራቸው አሉላ አባ ነጋ በንቡር ጠቃሽነት ተነስተዋል። ‹‹ስለጦቢያ የተነገረ ሽክም›› (84 — 85) በሚለው ግጥም ደግሞ፡- *የመሪዎችን ሀገር የመሸጥ ተግባር፣ በፈቃድ ስልጣን ያለመልቀቅና በአመጽ የመውረድ እጣ ፈንታን* ይገልጻል።

ደራሲው የኔ ዘመን ቃናው የጠፋበት ቅኝቱ የተበላሸበት ነው የሚለውን አመለካከቱን በግጥሞቹ አስተጋብቷል ብለናል። በመድብሉ የማሳረጊያ ገጾች ያሉትም ‹‹ጉደኛ ስንኞች›› እና ‹‹ሙሾ እና ባለቅኔ›› ህዝባዊ ግጥሞች ትኩረታቸው ሙሾ ነው። በአጠቃላይ ብዙዎቹ ግጥሞች ‹‹ሙሾ ነክ ግጥሞች›› ናቸው። የጀርባ ሽፋን መግለጫዎቹ ህዝባዊ ግጥሞችም ‹‹ሙሾ ቀመስ›› ናቸው። በአጠቃላይ ድርሰቶቹ የኑሮ መርግ ፣ ሰቆቃ፣ የተጫናቸው ነው።

## ማጠቃለያ

ከላይ እንዳየነው የበእውቀቱ የማለዳ ድባብ ግጥሞችን ላይ የተቀናጀ ውጫዊ እና ውስጣዊ ንባብ ለማድረግ ተሞክሯል። ይህም ማለት ግጥሞቹን በማንበብ ሂደት ሁኔተዎች ሲጋብዙ ከውጫዊ አውድ ማለትም ከማህበረፐሊቲካው ከታሪካዊው አውዶችና ከሌሎች ቴክስቶች ጋር በማቀናጀት ግጥሞቹን

**ለመረዳት ተሞክሯል፡፡ በዚህም የማለዳ ድባብ ግጥሞች የዘመኑን መንፈስ የሚገልጹ፣የአዲሱን ትውልድ መከራ የሚያስተጋቡ ግጥሞች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ገጣሚው/ተራኪው ይህን ሲያስተጋባ ደርግ ዳር ቆሞ ሳይሆን የመከራው ገፈት ቀማሽ ሆኖም ጭምር ድምጹን በማሰማት ነው፡፡**

**ይህን የትወልድ እሮሮ እና የሚያንገሸግሽ ኑሮ የገለጸው ደግሞ በደረቁ ሳይሆን እያስፈገገ ነው፡፡ በኮስታራ ድምጸት ሳይሆን በማዋዛት ነው፡፡ ቀላል ቋንቋ፣ ቀላል ቅንጅት በመጠቀም ነው፡፡ ንቡር ጠቃሽን ዘይቤን፣ ሽሙጥን በመጠቀም ነው፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ስለህይወትና ተፈጥሮ ያለውን ግንዛቤ ከፍልስፍና እያገናዘበ ነው፡፡**

## ዋቢ መጽሐፍት

**በዕውቀቱ ስዩም** (2009)፡፡ ***የማለዳ ድባብ፡፡*** **አዲስ አበባ፤ በዕውቀቱ ሥዩም፡፡**

Archer, J. (2009). The nature of human aggression. *International Journal of Law and Psychiatry*, 32, 202-20.

Heidegger, M, (1962). *Being and time* (Eng. Translation). Oxford: Blackwell Publishers Ltd.

Sisyphus. *World history encyclopedia.* https://www.worldhistory.org/sisyphus/

Time and Karma. https://www.pinterest.com/pin/670262357027136876/